የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አይሳኢታ ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት
ጠባቂነት የወጣ

2th year No 7
Aysaita- 8th July,1999

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ---------- ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 7/1991 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ

መንግስት ኃፊነቱን በትክክል መወጣት እንዲችል ዘመናዊ እና ቀልጣፋ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት ያለበት መሆኑ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የሚመራበትን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት አንቀጽ 47(2.2) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ #የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 7/1991 ;ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. #በዓይነት የተሰጠ ዕርዳታ; ማለት የክልሉ መንግስት ከገንዘብ ሌላ በእቃ ወይም በአገልግሎት መልክ በሁለት ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት ወይም ከሌሎች ምንጮች የሚቀበለው ማንኛውም እርዳታ ነው።
2. #መፍቀድ; ማለት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ለመክፈል የሚስችል በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጥ ማናቸውም ሥልጣን ነው።
3. #የካፒታል ወጪ; ማለት ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይም ለማሻሻል ወጪ የሚደረግ ሂሳብ ሲሆን ለምክር አገልግሎት የሚደረገውን ወጪ ይጨምራል።
4. #የተጠቃለለ ፈንድ; ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በማናቸውም 97106 ፕ 3 የመንግስት መ/ቤት ስም በክልሉ የፋይናንስ ቢሮ በተከፈለው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ የተደረገ የክልሉ መንግስት ገንዘብ የመንግስት መ/ቤቶች ለክፍያ እንዲውል በጥሬ የገንዘብ የያዙት እንዲሁም በዓይነት የተገኘ እርዳታ ነው።
5. #ግዴታ; ማለት በውል. በስምምነት ወይም በህግ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟ የሚፈጠር ኃፊነት ነው።
6. #ክፍያ; ማለት በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የተቀመጠውን የመንግስት ገንዘብ ወጪ ማድረግ ነው።
7. #የክልል መንግስት; ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።
8. #የበጀት ዓመት; ማለት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው ጊዜ ነው።
9. #የችሮታ ጊዜ; ማለት ባለፈው የበጀት ዓመት ርክክቡ ለተፈፀመ ዕቃ እና ለተሰጠ አገልግሎት ባለፈው የበጀት ዓመት ውስጥ የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ካለፈው ዓመት በጀት ላይ የሚከፈልበት ከሐምሌ 1 ቀን እስከ 30 ድረስ ያለው ቀናት ነው።
10. #መቅረት; ማለት ወጪ ለማድረግ የተሰጠው ፈቃድ ማብቅያ ጊዜ ነው።
11. #የቢሮ ኃላፊ እና ቢሮ; ማለት እንደቅደም ተከተሉ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ እና የፋይናንስ ቢሮ ነው።
12. #ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች; ማለት ከግብር እና ከመቀጫ በስተቀር ለክልሉ መንግስት ሊከፈል የሚገባ ማናቸውም ገንዘብ ነው።
13. #የመንግስት መ/ቤት; ማለት ማንኛውም በከፊል ወይም በሙሉ በክልል መንግስት በጀት የሚተዳደር መስሪያ ቤት ነው።
14. #የመንግስት ገንዘብ; ማለት የቢሮ ኃፊ ወይም ማናቸውም የክልሉ መንግስት ቢሮ ባለስልጣን ወይም ማናቸውም በክልሉ መንግስት ስም ገንዘብ ለመቀበል ወይም ለመሰብሰብ ስልጣን የተሰጠው ሰው የተቀበለው ወይም የሰበሰበው (ወይም በተሰብሳቢበት የያዘው) ማናቸውም የክልሉ መንግስት ገንዘብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል።

ሀ. የክልል መንግስት ልዩ ሂሳቦች እና ከእነዚህ የሚገኝ ገቢ

ለ. የክልል መንግስት ገቢዎች

ሐ. የክልል መንግስት የዋስትና ሰነዶችን በማወጣትና በመሸጥ የሚሰበሰበው ገንዘብ

መ. የክልል መንግስት ወይም ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በባለጉለት ወገን ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት ወይም ከሌሎች ምንጮች በብድር ወይም በእርዳታ የሚገኘው ገንዘብ

ሠ. ከፌደራል መንግስት የሚላክ የበጀት ድጋፍ

ረ. በዓይነት የሚገኝ እርዳታ

15. #የክልሉ መንግስት ንብረት; ማለት ከመንግስት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የክልል መንግስት ሀብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው፣
16. #ምህረት ; ማለት ግብርን መቀመጫን ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች መማር ወይም ነፃ ማድረግ ነው።
17. #እዳ መሰረዝ; ማለት የክልል መንግስት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ግዴታዎችን ወይም ሌላ የይገባኛል ጥያቄዎች ከሂሳብ መዝገብ መሰረዝ ነው።
18. #የዋስትና ሰነድ; ማለት የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈፀም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ነገር ሲሆን የግምጃ ቤት ሰነድን የተስፋ ሰነድንና ቦንድን ይጨምራል፣
19. #የጥሪት ፈንድ (ሲኒኪንግ) ፈንድ; ማለት በረጅም ጊዜ እንዲመለስ የተወሰደን ብድር ለመክፈል ቋሚ ንብረቶችን ለመተካት ወይም የክልሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያወጣው ደንብ ለሚወሰነው ሌላ ማናቸውም ዓላማ እንዲውል ኢንቨስት የሚዳረግ ገንዘብ ነው።
20. #የበጀት ድጋፍ; ማለት የፌደራል መንግስት ለክልል መንግስት የሚሰጠው ዓመታዊ የበጀት ድጋፍ ነው።
21. #ዝውውር; ማለት ከአንድ አርዕስት ንዑስ አርዕስት ፕሮጀክት ወይም የሂሳብ መደብ ወደ ሌላ የሚደረግ የተፈቀደ የበጀት ዝውውር ነው።
22. #የተለዬ ዓላማ; ማለት በህግ በተሰጠ ስልጣን መሰረት ተለይቶ በሚያዝ የመንግስት ገንዘብ የሚከናወን የክልል መንግስት ተግባር ነው።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ ተፈፃ የሚሆነው በመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ነው።
2. የክልል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አዋጁ የሚመለከታቸውን የመንግስት መስሪያ ቤቶች ዝርዝር በየጊዜው ያወጣል።

4. <u>ኃላፊነት እና ተጠያቂነት</u>

የእያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ የዚህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጡት ደንቦችና ድንጋጌዎች በሃላፊነት በሚመራው መ/ቤት ውስጥ ሙሉ በሙሉና በተገቢው መንገድ ተግባራዊ መሆናቸውም በማረጋገጥ ረገድ ለክልል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠያቂነት አለበት።

ክፍል ሁለት

የመንግስት ገንዘብ ስለ መሰብሰብና ገቢ ስለማድረግ

5. የተጠቃለለ ፈንድ

1. በተለየ ሁኔታ እንዲቀመጥ በህግ ከተፈቀደለት በስተቀር የክልሉ መንግስት ገንዘብ ሁሉ ገቢ የሚደረግበት አንድ የተጠቃለለ ፈንድ ይኖረዋል።
2. በዓይነት የተሰጠ እርዳታ ቢሮው ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር የሚያገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ በሚወሰነው ዋጋ መሰረት በተጠቃለለ ፈንድ ውስጥ ይመዘገባል።
3. ቢሮው የተጠቃለለው ፈንድ ይይዛል፣ ያስተዳድራል።
4. ቢሮው በማናቸውም የመንግስት መ/ቤት ስም የመንግስት ገንዘብ የሚቀመጥበት የባንክ ሂሳብ ሊከፈት ይችላል። የዚህ ዓይነቱም የባንክ ሂሳብ የተጠቃለለው ፈንድ አካል ይሆናል።

6. የመንግስት ገንዘብ አሰባሰብ

1. በህግ ካልተፈቀደ በስተቀር ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ መሰብሰብ አይቻልም።
2. ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ያለፋይናንስ ቢሮው ህጋዊ ደረሰኝ ሊሰበሰብ አይችልም
3. ማናቸውንም የመንግስት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበሰብ ስልጣን የተሰጠው ሰው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ገንዘብ የተቀበለበትን እና ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ መዝግቦ ይይዛል።

7. የመንግስት ገንዘብ ስለማስቀመጥ

1. በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ በመመዝገቡ በዚሁ እንደተቀመጠ ከሚቆጠር በዓይነት ከሚገኝ እርዳታ በስተቀር ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ በፋይናንስ ቢሮው ስም በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ይቀመጣል።
2. በተለየ ዓላማ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ ለዚሁ ዓላማ እንዲውል በሚፈቅደው አዋጅ መሰረት ወጪ ሆኖ ሊከፈል ይችላል።

8. ወለድ

1. ለተለየ ዓላማ እንዲውል በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ወለድ ሊከፈልበት ይችላል።
2. የወለዱ መጠን ቢሮው ከአስቀማጩ ጋር በመመካከር በሚያቀርበውና የክልሉ ምክር ቤት በሚያፀድቀው ልክ ይሆናል።
3. በቢሮው ወይም በማናቸውም የመንግስት መስሪያ ቤት ስም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም በንግድ ባንኮች በረከፈቱ የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ ላይ ሁሉ ባንኮቹ ወለድ ይከፍላሉ። የወለዱ መጠን በባንኩ እና በቢሮው መካከል በሚደረገው ስምምነት ይወሰናል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ዕዳን ስለመማር ስለመሰረዝ ስለ ልዩ ልዩ ክፍያዎች</u>

9. <u>የዕዳ ምህረት</u>

1. የክልል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በቂ ምክንያት መኑሩን ሲያምንበት ከቢሮው በሚቀርብለት አስተያየት መሰረት ከማናቸውም ግብር በዚሁ ላይ ከሚከፈል ወይም ከተከፈለ ወለድ ቅጮር ምህረት ሊያደርግ ይችላል።
2. ቢሮውን በበላይነት የሚመራው የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት በማናቸውም ግብር ላይ ከተጣለ መቀመጫ በዚሁ ላይ የሚከፈልን ወይም የተከፈለን ወለድ ቅጮር ምህረት ሊያደርግ ይችላል።
3. ቢሮው በበላይነት የሚመራው የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲያፀድቅለት ማናቸውንም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦችን እንዲሁም በዚሁ ላይ የተከፈለን ወይም የሚከፈልን ወለድ ቅጮር ሊምር ይችላል።

10. <u>ምህረት የሚደረግባቸው ሁኔታዎች</u>

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 9 በተደገገው መሰረት የሚደረግ ምህረት በሙሉ ወይም በከፊል በገደብ ወይም ያለገደብ ሆኖ ፣

ሀ. ታክስ መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለማስገባት ጉዳዩ ለክስ ከተመራ ክሱ ከተጀመረ ወይም ከጀመመሩ በፊት

ለ. ታክስ መቀጫ ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች በፍርድ አፈፃፀም ከመከፈላቸው በፊት ወይም ከተከፈሉ በኋላ

ሐ. ታክስን ወይም ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦችን የሚመለከት ማናቸውንም ጉዳይ ወይም ጉዳዮች ሲኖሩና የመክፈል ኃላፊነት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች ከመድረሳቸው በፊት ሊሰጥ ይችላል።

11. የተከፈለ ገንዘብን ስለመማር

በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ በማናቸውም አዋጅ መሰረት ምህረት የተደረገው በተከፈለ ገንዘብ ላይ ሲሆን ገንዘቡ ለዚሁ ዓላማ በተለይ ከተመደበው ሂሳብ ውስጥ ወጪ ተደርጎ ይከፈላል።

12. ምህረት የተደረገለት ዕዳ ሪፖርት ስለማድረግ

በዚህ አዋጅ ወይም በሌለካ በማናቸውም አዋጅ መሰረት በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ምህረት የተደረገለት ዕዳ ቢሮው በሚሰጠው መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ በሚቀርበው የመንግስት ሂሳብ ውስጥ ተጠቃሎ ሪፖርት ያደርጋል።

13. ዕዳን ስለመሰረዝ

1. ለክልል መንግስት መግባት ያለበት ማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሳብ መፈፀም ያለበት ግዴታ ወይም የይግባኝ ጥያቄ በሙሉ ወይም በከፊል ስለሚሰረዝበት ሁኔታ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ሊያወጣ ይችላል። እንደዚህ ያሉት ደንቦች፣

ሀ. ማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሳብ ግዴታ ወይም የይግባኝ ጥያቄ የሚሰረዝባቸውን መመዘኛዎች፣

ለ. ማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሳብ ግዴታ ወይም የክፍያ ጥያቄ ከመሰረዙ በፊት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና መፈፀም ስለሚገባው ስነ-ስርዓት እና

ሐ. የተሰረዙ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ግዴታዎችንና የይገባኛል ጥያቄዎችን በሚመለከት መያዝ ስለሚገባው መረጃዎችና መዝገቦች የሚያጠቃልሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

2. የማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ ግዴታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ መሰረዝ ከተፈቀደው በጀት ላይ የመቀነስ ውጤት የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ዕዳው ሊሰረዝ የሚችለው በበጀት አዋጅ ወይም በሌላ ማናቸውም ኣጅ በወጪ በጀት የተያዘ ሲሆን ብቻ ነው።

3. የማንኛውም ተሰብሳቢ ሂሳብ ግዴታ ወይም ሌላ የይገባኛል ጥያቄ መሰረዝ የክልሉ መንግስት ዕዳውን በማስመለስ ወይም ለመሰብሰብ ያለውን መብት አይገድብም።

4. ማንኛውም በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ አዋጅ መሰረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተሰረዘ ተሰብሳቢ ሂሳብ ግዴታ ወይም ሌላ የይገባኛል ጥያቄ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ የመንግስት ሂሳብ ውስጥ ተጠቃሎ ሪፖርት መደረግ አለበት።

14. የአገልግሎት ክፍያዎች

1. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት ዕቃ ለሚሰጡት አገልግሎት እና ለአገልግሎት መስጫዎች የሚያስከፍሉትን ዋጋ ልክ በሚመለከት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በተመለከተ ሌላ አዋጅ ልዩ ስልጣን የተሰጠ ከሆነ በንዑስ አንቀፁ የተመለከተው ተፈፃሚ አይሆንም ።

አንቀጽ አራት

በጀት

15. የአቀራረብ ሥርዓት እና ጣሪያ

1. ቢሮው እና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አግባብ ካለው የመንግስት ባለስልጣን ጋር በመመካከር ዓመታዊ በጀት ስለሚቀርብበትና ለእያንዳንዱ የበጀት ጥያቄ መሰረት ሊሆን ስለሚገባው ከፍተኛ የገንዘብ መጠን የበጀት አቀራረብ ስርዓት ይቀርፃሉ።
2. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የተከታታይ ዓመታት የመንግስት ኢንቨስትምንት ፕሮግራሞች የአቀራረብ ስርዓት ይመሰርታል።

16. በጀትን ስለማጽደቅና ስለማሳወቅ

ለዓመቱ የተፈቀደው በጀት እስከ ሰኔ 30 ቀን በክልሉ ምክር ቤት ጸድቆ ሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች እስከ ሀምሌ 7 ቀን እንዲያውቁት ይደረጋል።

17. የበጀት ዝውውር

1. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ከመደበኛ ወደ ካፒታል በጀት ማዛወር ይቻላል።
2. ከካፒታል በጀት ወደ መደበኛ በጀት ማዛወር ይቻላል።

18. በመንግስት መ/ቤት ውስጥ የሚደረግ በጀት ዝውውር

1. በመንግስት መ/ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር መደበኛ በጀትን በሚመለከቱ በዋና ሂሳብ መደቦችውስጥ የሚደረግ ዝውውር እስከሆነ ድርስ የቢሮው ኃላፊ በጀትን ለማዛወር ያውን ስልጣን በውክልና አግባብ ላለው የመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል።
2. የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሃላፊ በጀትን ከአንድ የካፒታል ፕሮጀክት ወደ ሌላ የካፒታል ፕሮጀክት ለማዛወር ያለውን ስልጣን በውክልና አግባብ ላለውወ የመንግሰት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሰጥ ይችላል።

19. በመንግሰት መ/ቤቶች መካከል የሚደረግ የበጀት ዝውውር

የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግስት መ/ቤት የካፒታል በጀት ወደሌላ የመንግስት መ/ቤት የካፒታል በጀት እንዲዘዋወር ሊፈቅድ ይችላል።

ሀ) በመንግስት መ/ቤት የፀደቀ መዋቅር ለውጥ ወይም የስራ ኃላፊነት መሻሻያ በመደረጉ ምክንያት የበጀት ዝውውር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ

ለ/ በአንድ የመንግስት መ/ቤት ውስጥ ያጋጠመን የካፒታል በጀት እጥረት ለማቃለል ለሌላ የመንግስት መ/ቤት የተፈቀደ የካፒታል በጀት በማዘዋወር መጠቀም አስፈላጊ ሲሆንና ይህም ተጨማሪ በጀት ያስፈለገው ቀደም ሲል ለተፈቀደ የካፒታል በጀት መሆኑ ሲረጋገጥ

20. ለድንገተኛ ወጪ ስለሚደረግ የበጀት ዝውውር

በዓመቱ የበጀት አዋጅ የተቀመጠው ማናቸውም ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በስራ ላይ ላለው በጀት ዓመት የስራ እንቅስቃሴ በጣም አስቸኳይ የሆነና የዓመቱ በጀት በሚዘጋ በጀት ጊዜ ያልታሰበ ተጨማሪ ገንዘብ ሲጠየቅ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለድንገተኛ ወጪ የሚሆን በጀት ማዛወር ይችላል።

21. የበጀት መፅደቅ መዘግየት

1. የክልሉ ምክር ቤት በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የዓመቱን በጀት ሳያፀድቀው ሲቀር መክር ቤቱ የዓመቱን በጀት እስኪያፀድቀው ባለፈው ዓመት የጸደቀው መደበኛ በጀት ቤወሩ እየታየ ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቀደም ሲል ለተፈቀዱ የካፒታል ፕሮጀክቶች ክፍያ ሊፈፀም የሚችለው ከፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር ይሆናል።

ክፍል አምስት

የመንግስት ገንዘብ ክፍያ

23. ከተጠቃለለው ፈንድ ክፍያ ስለመፈፀም

አንቀጽ 22 እንደተጠበቀ ሆኖ

1. የክልሉ ምክር ቤት በበጀት ካልፈቀደ በስተቀር ከተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ክፍያ ለመፈፀም አይቻልም።

2. በቢሮው ካልጸደቀው በስተቀር ከፈቀደው በጀት ላይ ክፍያ መፈፀም ወይም የክፍያ ግዴታ መግባት አይቻልም፡

24. የክፍያ ገደብ

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 16-21 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከቱት መንግስት መ/ቤቶች እንዲከፈል ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈፀም አይቻልም።

25. ግዴታ ስለመግባት

1. በመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው በጽሁፍ ካልጠየቀ በስተቀር ለመ/ቤቱ ከተፈቀደው በጀት ላይ ክፍያ ለመፈፀም ግዴታ መግባት አይቻልም።
2. ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሚደርስ ማናቸውም ዕዳ ለመክፈል የሚያስችል በቂ በጀት ካልኖረው በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ ክፍያን የሚጠይቅ ስምምነት ወይም ሌላ ዓይነት ግዴታ ውስጥ መግባት አይቻልም።
3. ቢሮው ለእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ የተገባለትን የፋይናንስ ግዴታ ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓትና የሚመዘገብበት ቅጽ ያወጣል።
4. የመንግስት መ/ቤት የበላይ ሃላፊ ቢሮው በሚያወጣው ቅጽ መሠረት ለእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ የተገባለትን ግዴታ ለመቆጣጠር የሚያስችል መዝገብ ይይዛል።

26. ለዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚደረግ ክፍያ

1. መቅረብ ካለበት የወጪ ዝርዝር ወይም የክፍያ ማረጋገጫ በተጨማሪ የመንግስት መ/ቤት የበላይ ሃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ካላረጋገጠ በስተቀር ክፍያ ሊፈፅም አይችልም።

ሀ). የተከናወኑ ስራዎች የእቃዎችና አገልግሎት አቅርቦት ክፍያዎችን የሚመለከት ሲሆን

i. ስራው መጠናቀቁን ዕቃው መቅረቡን ወይም አገልግሎቱ መሰጠቱንና ዋጋው በስምምነቱ መሠረት የተጠየቀ መሆኑን ዋጋው በስምምነቱ ካልተገለጸም ተቀባይነት ያለው መሆኑን

ii. በስምምነቱ በተገባው ግዴታ መሠረት ክፍያ የሚፈፀመው ስራው ከመጠናቀቁ ዕቃው ከመቅረቡና አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ሲሆን ክፍያው በስምምነቱመሠረት የተጠበቀ መሆኑ ወይም

iii. ቢሮው በሚያወጣው ስርዓት መሰረት ማረጋገጫ ከመገኘቱ በፊት ክፍያ መፈፀም ያለበት ሲሆን ጥያቄው ተቀባይነት ያለው መሆኑን ወይም

ለ). ማናቸውም ከዚህ ወጪ የሚደረግ ክፍያ ሲሆን የሚከፈለው ሰው ክፍያውን ለማግኘት የሚገባው መሆኑን

2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ መሠረት ሊሟላ የሚገባውን የማረጋገጥና የማጣራት አፈጻፀም ስርዓት ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

27. በበጀት ዓመት መጨረሻ የሚሰጥ የትርፍታ ጊዜ

እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለቀረበለት የክፍያ ጥያቄ የበጀት ዓመቱ ባለቀ 30 ቀናት ውስጥ፦

ሀ. የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለታዘዙና ለተረከባቸው እቃዎች

ለ. የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለታዘዙና ለተሰጡ አገልግሎቶች እና

ሐ. የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ማናቸውም የክፍያው ጊዜ የደረሰ ወይም በውል በተገባው ግዴታ መሰረት መከፈል ያበትን መዋጮ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ግዴታ መከፈል አለበት።

28. የካፒታል በጀት የሚታይበት ልዩ ሁኔታ

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 27 የተመለከተው ቢኖርም የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ክፍያውን ያፀደቀው ከሆነ የካፒታል ወጪ የበጀት ዓቱ ባለቀ በ 30 ቀናት ውስጥ ሊፈፀም ይችላል።

ክፍል ስድስት

ስራ ላይ ያልዋለው በጀት አስተዳደር

29. ስራ ላይ ያልዋለ በጀት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 እና 28 የተመለከተቱት እንደዚሁም ቢሮው ስለጉዳዩ የሚያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደ እና ወጪ ሳይደረግ ወይም ስራ ላይ ሳይውል የቀረ ሂሳብ ሁሉ ስራ ላይ መዋሉ ቀርቶ ለቢሮው የትሬዠሪ ፈሰስ ይደረጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም የእርዳታና የብድር ሂሳብ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ስራ ላይ መዋሉ ሊቀጥል ይችላል።

30. የቅድሚያ ክፍያ

በተሰጠበት የበጀት ዓመት መጨረሻ ያልተመለሰ፣ ያልተወራረደ ወይም ያልተተካ ማናቸውም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በዓመቱ ከሚቀርበው የመንግስት ሂሳብ ጋር ተጠቃሎ ሪፖርት መደረግ አለበት።

31. ስለመቻቻል

ማናቸውም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በእንዲህ ያለውን ክፍያ በሚያዘው ደንብ መሰረት በሙሉ ወይም በከፊል ያልተከፈለ ያልተወራረደ ወይም ያልተመለሰ ሲሆን፣

ሀ. ከጡረታ አበል በስተቀር የቅድሚያ ክፍያውን ለወሰደው ሰው በክልሉ መንግስት ከሚከፈል ማናቸውም ገንዘብ

ለ. የቅድሚያ ክፍያውን የወሰደው ሰው ሞቶ እንደሆነ ከጡረታ አበል በስተቀር ለወረሾቹ ከክልሉ መንግስት ከሚከፈል ማናቸውም ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ ይችላል።

32. የወጪ ተመላሽ

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የክልሉ መንግስት የተቀበለው ማናቸውም

1. የወጪ ተመላሽ
2. የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ
3. በብልጫ የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ
4. በተመላሽ ሂሳብ በተመላሽ ታክስ ወይም ላይ ክፍያ ላይ የዋጋ ማስተካከያ በመደረጉ ምክንያት የሚገኝ ተመላሽ ጭምር
5. የጉዳት ካሳ በመክፈሉ ምክንያት የተገኘ ገንዘብ ወይም
6. በመንግስት መ/ቤት ሃብት ላይ የደረሰው ጉዳት ወይም ኪሳራ እንዲተካ በቀረበ ጥያቄ ምክንያት የሚገኝ ገንዘብ ቀደም ሲል ለዚሁ ጉዳይ የተደረገው ወጪ ወይም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በተያዘበት የበጀት ርዕስ ገቢ ሆኖ መመዝገብ አለበት።

ክፍል ሰባት

የክልሉ መንግስት ዕዳ

33. የመበደር ስልጣን

የፌዴራል መንግስት የሚወሰነው የብድር ገደብ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 እና 36 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ካልፈቀደ በስተቀር በክልሉ መንግስት ወይም በክልሉ መንግስት ስም ገንዘብ ለመደበር ወይም ዋስትና ለመስጠት አይቻልም።

34. ገንዘብ የማሰባሰብ ስልጣን

1. የክልሉ መንግስት ወይም በክልሉ መንግስት ስም ገንዘብ ለማሰባሰብ ስልጣን ሲሰጥ ገንዘቡን ለማሰባሰብ በሚፈቀደው አዋጅ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዚሁ አዋጅ መሰረት ገንዘቡ በሙሉ ወይም በከፊል በቀጥታ ብድር ወይም በዋስትና ሠነድ አማካኝነት እንዲሰባሰብ ሊፈቅድ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ለማከናወን እንዲቻል የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የቢሮው ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው ሌላ የቢሮው ባለስልጣን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እንዲፈጽም ስልጣን ይኖረዋል።

ሀ. ሠነዱ የሚወጣበትንና ዕዳው ተከፋይ የሚሆንበትን ቀን እና የዕዳው ን አከፋፈልና የወለዱን መጠን ለመወሰን፣

ለ. የዋስትና ሠነዶችን እንደአስፈላጊነቱ ለመሸጥ

ሐ. የቀጥታ ብድር ወይም የዋስትና ሠነዶችን ማውጣትና መሸጥን በሚመለከት ስምምነት ለመፈፀም እንደገና ለመደራደር

መ. በቢሮው ሁኔታዎች የብድሩን ገንዘብ በከፊል ወይም በሙሉ መልሶ ለማበደር

35. ቀጥታ ብድሮችን ወይም የዋስትና ሠነዶችን ለመክፈል ስለሚወሰድ ብድር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የክፍያው ጊዜ የደረሰ ወይም ተመላሽ እንዲደረግ ጥያቄ የቀረበበትን የቀጥታ ብድር ወይም የዋስትና ሠነድ ክፍያ ለመፈፀም የሚያስችል ገንዘብ መበድር እንዲችል ለቢሮው ኃላፊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

36. ለተጠቃለለው ፈንድ አስተዳደር ስለሚወሰድ ብድር

የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተጠቃለለውን የመንግስት ፈንድ በበቂ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያስችል ገንዘብ እንዲበደር ለቢሮው ኃላፊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

37. ጊዜያዊ ብድሮች

የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በህግ የተፈቀዱለትን ክፍያዎች ለመሸፈን የተጠቃለለው ፈንድ በቂ መስሎ ሳይታየው ሲቀር የተጠቃለለው ፈንድ ለክፍያዎቹ ሊበቃ ይችላል ብሎ ከሚያምንበት የገንዘብ መጠን የማይበልና ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ተመልሶ የሚከፈል ገንዘብ እንዲበደር ለቢሮው ኃላፊ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

38. የእዳ ገደብ

በሌላ አግባብ ባለው አዋጅ የተደነገገ ገደብ ሳይቃረን የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በቀጥታ በመበደርም ሆነ ዋስትና በመስጠት የክልሉ መንግስት ከአገር ውስጥ ሊበደረር የሚችለው ዕዳ መጠን ይወሰናል።

39. የብድር ግዴታዎች ክፍያ

በክልሉ መንግስት ወይም በክልሉ መንግስት ስም የተወሰዱ ቀጥታ ብድሮች እና የዋስትና ሰነዶች ዋና ገንዘብ በዚሁ ላይ የሚከፈል ወለድ እና የአስተዳደር ወጪ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ የሚታሰብ ሆነው ከዚሁ ወጪ ተደርገው ይከፈላሉ።

40. ኪሣራ

የቢሮው ኃፊ፦

1. የዋስትና ሠነዶቹን የመግዣ ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል ከፍለው ዋስትናው ወይም የከፈሉበት ገንዘብ ያልተመለሰላቸው በመሆኑ በገንዘብ ከፋዮቹ ላይ የደረሰውን ማናቸውም ኪሳራ እና
2. የዋስትና ሠነዱን ለማስመለስ በማናቸውም ሰው ላይ የደረሰውን ኪሳራ ከተጠቃለለው ፈንድ ወጪ አድርጎ ሊከፍ ይችላል።

41. ዋስትና

1. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከሚያወጣቸው ደንብ ጋር የማይቃረን እስከ ሆነ ድረስ የክልሉ መንግስት ለግዴታ መፈፀም ዋስትና ሊሰጥ ይችላል።
2. ዋስትናን በሚመለከት የሚደረግና ክፍያ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ጪ ተደርጎ ይከፈላል።

42. የመንግስት ዕዳ አስተዳደር

የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የክልሉን መንግስት ዕዳ ስለ ማስተዳደር በዚሁ እዳ ላይ ወለድ ስለሚከፈልበት ሁኔታ እንዲሁም ለዋስትና አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

43. የክልል መንግስት ዕዳ ስለማስተላለፍ

1. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የክልሉ መንግስት ዕዳ ስለሚተላለፍበት ሁኔታ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
2. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሶስተኛ ወገኖች ዕዳን ለክልሉ መንግስት ሊያስተላልፍ ስለሚችሉበት ሁኔታ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ዕዳ ሊተላለፍ አይችልም።

44. የመንግስት ዕዳ ስለመመዝገብ

ቢሮው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በሚመለከት የተሟሉና ዝርዝር የሆኑ መዛግብት ይይዛል።

1. በክልሉ ምክር ቤት በተሰጠው ፈቃድ ቀጥታ ብድሮችን እና የዋስትና ሠነዶችን በማውጣትና በመሸጥ ብድር የተወሰደበትን ገንዘብ፣
2. በዚህ አይነት ብድር የተገኘ ገንዘብ መግለጫ
3. በብድር የተገኘውን ገንዘብ በሚመለከት የተከፈለ ዋና ገንዘብ እና ወለድ፣
4. ቀጥታ ብድሮች እና ዋስትና ሠነዶችን ከማውጣት ከማስተዳደር እና ከመክፈል ጋር በተያያዘ ለሚሰጡ አስተዳደራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም ዋስትናዎችን መስጠትን ማስተዳደርና መክፈልን በሚመመለከት ለተደረጉ አስተዳደራዊ አገልግሎቶች ለፊጂስራሮች፣ ለፋይናንስ ወኪሎች እና ሌሎች የተከፈለውን ገንዘብ መጠን፣
5. ዋስትናዎችን በሚመለከት የተፈቀዱበትን ስለዋስትናው መግለጫ የተከፈለውን መጠንና ጠቅላላ የአስተዳደር ወጪዎች፣

ክፍል ስምንት

የመንግስት ገንዘብ ኢንቨስት የማድረግ ስልጣን

45. የተረፈ ፈንድ ኢንቨስትመንት

የቢሮው ኃላፊ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ የሚገኘው ገንዘብ ለጊዜው ለክፍያ የማይፈለግ ሲሆን ይህንን ገንዘብ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያወጣው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተገቢ ናቸው በሚላቸው የዋስትና ሰነዶች ላይ ኢንቨስትመንት ሊያደርግ ይችላል።

46. የጥሪት ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር

1. የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የጥሪት ፈንድ የሚቋቋምበትንና የሚተዳደርበትን ሁኔታ ይወስናል።
2. በጥሪት ፈንድ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ወጪ ሆኖ ይከፈላል።

ክፍል ዘጠኝ

የክልሉ መንግስት ንብረት

47. ስለመያዝና ስለማስወገድ

በሌሎች አዋጆች የተደነገገው እንደተተበቀ ሆኖ የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ካልሆነ በስተቀር የክልሉን መንግስት ንብረት በመያዝ ወይም ማስወገድ አይቻልም።

48. የንብረት ጥበቃና ቁጥጥር መዘግብት

እያንዳንዱ የመንግስ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ቢሮው ስንብረት ጥበቃና ቁጥጥር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በመ/ቤቱ ኃፊነት ስር የሚገኘውን የመንግስት ንብረት በሚመለከት ጥበቃ ያለው መዝገብ መያዝ አለበት።

ክፍል አስር

የመንግስት ሂሳብ

49. የሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ

ቢሮው የእያንዳንዱየበጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት በተቻለ ፍጥነት ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል።

50. የሪፖርቱ ይዘት

የመንግስት ሂሳብ ሪፖርት የሚቀርበው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሆኖ የሚከተሉትን ካታትታል።

1. የሂሳብ መግለጫዎች

ሀ. የበጀት ዓመቱ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች

ለ. የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመቱ ገቢዎችና ወጪዎች፣

ሐ. የተጠቃለለው ፈንድ

መ. የክልሉ መንግስት ዕዳዎች ዋስትና የተገባባቸውና የሚጠበቁ ግዴታዎች

ሠ. ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው ወጪ የተደረገውን እና ወጪ ያልተደረገውን የገንዘብ መጠን፣

ረ. የዘቀጠ ፈንድ ካለ ይህንኑ

ሰ. የክልሉን መንግስት የበጀት ዓመቱን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች እና አቋም የሚያሳዩ ሌሎች ሂሳቦችና መረጃዎች፣

2. የክልል ኦዲት ጽ/ቤት የክልን መስግስት የፋይናንስ መግለጫ መርምሮ የሰጠውን አስተያየት፣
3. አግባብነቱ በቢሮው የታመነበት ሌላ ተመሳሳይ መረጃ፣

51. <u>የገንዘብ አይነት</u>

የክልሉ መንግስት ሂሳብ ሚያዘውና ሪፖርት የሚደረገው ኢትዮጵያ ብር ይሆናል።

52. <u>መዛግብት</u>

1. የያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት ኃፊ ቢሪው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የመ/ቤቱን ኃላፊነት የሚመለከቱ የፋይናንስ መዝገቦችን ይይዛል ለቢሮውም ያቀርባል።
2. እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ሂሳቡን ዘግቶ ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል።

ክፍል አስራ አንድ

ግዥና ውሎች

53. ውሎች ስለሚገዙባቸው ደንቦች

ክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስለውሎችና ክፍያ አፈፃፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል። ይህም ደንብ ስለግዥና ስለውሎች አፈፃፀም ለውሎች ስለሚሰጠው ዋስትና እና የውሉን አፈፃፀም ማስከበሪያ የሆኑ ድንጋጌዎችን የሚያካትት ሊሆን ይችላል።

54. የውል ግዴታ

1. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳያረጋግጥ የክልሉ መንግስት የሚገደድበት ውል መፈፀም የለበትም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አፈፃፀሙ ከአንድ የበጀት ዓት በላይ ለሚወሰድ ፕሮጀክት የረዥም ጊዜ ውል ለመዋዋል ለፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ዓት የተፈቀደ በጀት መኖሩን ማረጋገጥ ብቻ በቂ ይሆናል።

55. የግዥ አፈፃፀም

የማናቸውም ዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈፀም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል። ይህም መመሪያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስለሚገዙበትና ግዥው ለህዝብ ግልጽ ስለሚደረግበት ሁኔታ ዝርዝር መረጃዎችን የሚይዝ መሆን አለበት።

56. የግዥ ደንቦችን ወቅታዊነት ስለማረጋገጥ

ቢሮው ከክልሉ መንግስት ግዥና ውሎች ጋር የተያያዙ የዐስተዳደር ፖሊሲዎችንና ደንቦች በየጊዜው መውጣታቸውንና በሰፊው መሰራጨታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

ክፍል አስራ ሁለት

የፊደራላዊ መንግስትና የክልሉ መንግስት የፋይናንስ ግንኙነቶች

57. ጠቅላላ

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስትና በክልሉ መንግስት መካከል የሚኖረው የፋይናንስ ግንኙነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ለክልሉ የሚሰጠውን ዓመታዊ የበጀት ድጋፍ ይጨምራል።
2. የክልሉ መንግስት ከፌዴራላዊ መንግስት የሚቀርበውን የበጀት ድጋፍ ድንማ በሚመለከት በፌዴራሉ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት ሂሳቡን ይይዛል። ለፌደራሉ መንግስት ሪፖርት ያቀርባል።

58. የአገር ውስጥ ብድር

1. የፌዴራሉ መንግስት ክልሉ ሊበደር የሚለውን የገንዘብ መጠን መወሰን እንዲችል የክልሉ መንግስት ለፌዴራሉ መንግስት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ መስጠት አለበት።
2. የክልሉ መንግስት የሚወስደው ብድር የተገኘው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውጪ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውንም በብድር ከተገኙ ገንዘብ ላይ ሚፈፀም ክፍያ የኢትዮጵ ብሔራዊ ባንክ የሚያስተዳድረው ይሆናል።
3. የክልሉ መንግስት የሚወስደው ብድር ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውጪ የተገኘ ሲሆን የክልሉ መንግስትና የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ሚኒስቴር በጋራ የሚስማሙበት የአስተዳደር ስርዓት ተፈፃሚ ይሆናል።

59. የውጭ ምንዛሬ

ቢሮው የክልሉ መንግስት የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት በሚመለከት ለፌዴራሉ መንግስት የገንዘብ ሚኒስቴር ተገቢውን መረጃ መስጠት አለበት።

ክፍል አስራ ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

60. መመሪያዎች

ቢሮው ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

61. ስለ መንግስት ገንዘብና ንብረት መጥፋት

የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከቢሮው የሚያገኘውን አስተያየት መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ላይ ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

ሀ. በማንቸውም መንገድ የመንግስት ገንዘብ ወይም ንብረት ሲጠፋ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች

ለ. የጠፋው የመንግስት ገንዘብ ከተፈቀደው በጀት በላይ ስለሚቀነስበት ሁኔታ፣

ሐ. ከዚህ በላይ በፌደል ሀ የተመለከተው ማናቸውም የጠፋ የመንግስት ንብረት ወይም ገንዘብ በመንግስት ሂሳብ ውስጥ ሪፖርት የሚደረግበትን ሁኔታና ስለሚመዘገብበት መንገድ፣

62. <u>ጥፋቶችና ቅጣቶች</u>

1. የመንግስት ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ለማስተዳደር ወይም ክፍያ ለመፈፀም በማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የተቀጠረ የመንግስት ሠራተኛ ወይም ተሿሚ

ሀ. በህግ መሰረት ሊከፈለው ከሚገባ በቀር የተመደበበትን ስራ በማከናወኑ ማናቸውንም ክፍያ ከተቀበለ፣

ለ. የክልሉን መንግስት ገንዘብ በማጭበርበር ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣

ሐ. በሌላ ማናቸውም ሰው ህጉ እንዲጣስ ሆን ብሎ የፈቀደ፣

መ. ገቢን በመመዝገብ ወይም የምስክር ወረቀት በመስጠት ስራ ላይ የተሰማራ ሆኖ ሳለ በፈቃድኝነት በማቸውም መንገድ ሀሰተኛ የሆነ መረጃን በመዝገብ ለይ ያሰፈረ ሀሰተኛ የምስክር ወረቀት የፈረመ ወይም ያዘጋጀ፣

2. እንደሆነ ከብር 25.000 ሺ በማያንስና ከብር 35.00 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ 10 አመት በማያንስ ከ 15 አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
3. የመንግስት ገንዘብ ለመሰብሰብ ፣ ለማስተዳደር ወይም ክፍያ ለመፈፀም በማናቸውም የመንግስት መስሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው ማንኛውንም ክፍያ ለማስቀረት ወይም መጠኑን ለማሻሻል ወይም በህግ መጣሱን በሚመለከት የሚቀርቡ የክስ አቤቱታዎችን ለማስቀረት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በስጦታ ወይም በሌላ መልክ ገንዘብ ወይም ዋጋ ያለው ነገር እንዲሰጠው የተጠየቀ የተቀበለ ወይም ለመቀበል የሞከረለ እንደሆነ ከብር 25.000 ሺ በማያንስና ከብር 35.00 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ 10 ዓመት በማያንስ ከ 15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
4. የመንግስት ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ለማስተዳደር ወይም ክፍያ ለመፈጸም በማናቸውም የመንግስት መስሪያ ቤት የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችን የመተላለፍ ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጠሙን እያወቀ ለበላይ ኃላፊዎች ሪፖርት ያላደረገ እንደሆነ ከብር 10 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ 15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 የተደነገገው በመተላለፍ የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳያረጋግጥ ማንኛውንም ውል የተፈራረመ ወይም እንዲፈረም ያደረገ የመንግስት መስሪያ ቤት ኃላፊ ከብር 25.000 ሺ በማያንስ ከብር 15 ሺ በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

6. ማናቸውም ሰው የመንግስት ገንዘብ ከመሰብሰብ ከማስተዳደር ወይም ክፍያን በመፈፀም ስራ ላይ በተሰማራ የመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ የተሾመ ወይም የተመደበ ሰው፣

ሀ. የቀረበለትን ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉዳይ ወይም በስራ ኃላፊነቱ ምክንያት ሊቀርብለት በሚችል ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ወይም የሚወሰደውን እርምጃ ለማዛባት ወይም

ለ. በመንግስት ገቢ ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈፀም ወይም ድርጊቱ ሲፈፀም ሁኔታዎች ለማመቻቸት ወይም እንዲፈቅድ ለማድረግ ለማሰብ፣

ሐ. ጉቦ ለመስጠት ቃል ከገባለት ካቀረበለት ወይም ከሰጠው ጥፋተኛ ሆኖ መገኘቱ ሲያረጋግጥ በጉቦ መልክ ያቀረበውን ወይም የሰጠውን ገንዘብ ሶስት እጥፍ የገንዘብ መቀጮ እና ከ 10 ዓመት በማያንስ እና ከ 15 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

7. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን ጥፋቶች በመፈፀም ተግባር ውስጥ የተሳተፈና ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ጥፋት እና ስለተባባሪዎችቹ ሚና ጠቃሚ መረጃ የሰጠ ሰው በዚህ ህግ መሰረት ከሚቀርብበት ክስ በፍትህና አቃቤ ህግ ቢሮ ምህረት ሊደረግለት ይችላል።

63. <u>የሂሳብ ሠነዶችን ስለማየት</u>

1. ቢሮው በህግ የተሰጠውን ኃፊነት ለመወጣት የማናቸውንም የመንግስት መ/ቤት የሂሳብ መዛግብቶች መጽሃፈት ወረቀቶች የሂሳብ ሰነዶች እና መረጃዎች ለማት ያልተገደበ ስልጣን አለው።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 1 የተመለከተው ቢኖርም ለክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ሪፖርት ያያደርጉ የመንግስት መ/ቤቶች የሒሳብ መዛግብትን ወረቀቶችን የሂሳብ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ቢሮው ለማየት የሚችለው ከነዚህ የመንግስት መ/ቤቶች ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል።

64. <u>የውክልና ስልጣን ስለመስጠት</u>

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የቢሮው ኃላፊ ለመ/ቤቱ ባለስልጣኖች ወይም ለሌሎች ቢሮዎች ባለስልጣኖች ስልጣኑን በውክልና ለመስጠትና ውክልና ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን ይችላል።

65. <u>ሰነዶችን ስለመጠበቅ</u>

የክልሉን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እያንዳንዱ የሂሳብ ሰነድ መጠበቅ ያለበት ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ የሚገልፅ ደንብ ያወጣል።

66. <u>የተሻሩ ህጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ ደንብ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

67. <u>የመሸጋገሪያ ውሳኔ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13፣14፣17፣41፣42፣43፣45፣47፣53፣61 እና 65 የተደነገጉ ቢኖሩም የክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ እስከሚያወጣ ድረስ እነዚህ ጉዳዮች በተመለከተ በስራ ላይ የሚገኙ መመሪያዎች እና አሠራሮች ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ ካልሆኑ በስተቀር ተፈፃሚ ይሆናሉ።

68. <u>የተፈፃሚነት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር